የሰ/መ/ቁጥር---238299
ቀን- ሕዳር 28 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

አመልካቾች:- 1. ወ/ሮ አስካለ ጫላ
2. ወ/ሮ አለሚ ጫላ — ጠበቃ ሰለሞን ምስጋናው ቀረቡ
3. አቶ ማሞ ጫላ

ተጠሪ፡- አቶ መንግስቱ ረጋሳ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የገጠር መሬት ይዞታ ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በአደአ በርጋ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት አመልካቾች ከሳሾች ሲሆኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበዉ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 402791 ጥቅምት 22 ቀን 2015 ዓ.ም የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

አመልካቾች በተጠሪ ላይ ያቀረቡት የክስ አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፡- አያታቸዉ አቶ ረጋሳ ገቢሳ ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም እንዲሁም አያታቸዉ ወ/ሮ ነዲ ሆራ ሐምሌ 05 ቀን 2011 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆናቸዉን፤ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች 3 ሲሆኑ የአመልካቾች አባት የሆነዉ አቶ ጫላ ረጋሳ በ1984 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ በመሆኑ አባታቸዉን ተክተዉ የአያቶቻቸዉን የመሬት ይዞታ ሊወርሱ የሚገባ ቢሆንም ተጠሪ ሊያካፍላቸዉ ፍቃደኛ ባለመሆኑ በክሳቸዉ ላይ ከተራ ቁጥር 1ኛ እስከ 11ኛ የተጠቀሱ የመሬት ይዞታዎችን እንዲያካፍላቸዉ እንዲሁም ከ12ኛ እስከ 15ኛ የተገለጹ ንብረቶች ግምት ዉስጥ የእያንዳንዳቸዉ ድርሻ ብር 6,388.67 እንዲሁም የጥማድና ንብረት ግምት ብር 5,700 እንዲከፍላቸዉ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

የአሁን ተጠሪም ለቀረበባቸዉ ክስ የሰጡት መልስ ይዘት፡- የአመልካቾች አባት የሆነዉ ሚች አቶ ጫላ ረጋሳ ከወ/ሮ ነዲ ሆራ አልተወለደም፡፡ አመልካቾች የገጠር መሬት ይዞታን በክልሉ የገጠር አዋጅ መሠረት በዉክልና ለመዉረስ መብት የላቸዉም፡፡ አመልካቾች በዉክልና ይወረሳሉ ቢባል እንኳ የአያታቸዉን ድርሻ ብቻ ለይተዉ መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡፡ በ3ኛ ተራ ቁጥር በክሳቸዉ የገለጹት ባህር ዛፍ በ2003 ዓ.ም በተደረገ የስጦታ ዉል ለተጠሪ ተሰጥቷቸዉ ከ10 ዓመት በላይ ሲጠቀሙበት የቆዩትና በ2011 ዓ.ም ጋብቻ ሲፈጽም በጋብቻ ዉል ተቆጥሮ የተዳረበት በመሆኑ ሊጠይቁት እንደማይገባ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

የአደአ በርጋ ወረዳ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ፤ ማስረጃዎችን ሰምቶና መርምሮ፡- የአመልካቾች አባት ከወ/ሮ ነዲ ሆራ ያልተወለዱ በመሆናቸዉ አመልካቾች የወ/ሮ ነዲን የዉርስ ድርሻ ሊወርሱ አይችሉም፤ እንዲሁም የወንድ የአያታቸዉን ዉርስ ሀብት በተመለከተ የቤተሰብ አባል ባለመሆናቸዉ አባታቸዉን ተክተዉ የገጠር መሬት ይዞታዎችን ሊወርሱ አይችሉም፤ ሊወርሱ የሚችሉት የአያታቸዉን የንብረት ግምትን አስመልክቶ አባታቸዉን ተክተዉ በመሆኑ ተጠሪ ለአመልካቾች ለእያንዳንዳቸዉ ብር 2,766.66 እንዲከፍል ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካቾች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮና መርምሮ ምንም እንኳ አመልካቾች የአያታቸዉ የቤተሰብ አባል ባይሆኑም የአያታቸዉን የገጠር መሬት ይዞታ አባታቸዉን ተክተዉ እንዳይወርሱ የክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ የሚከለክል ባለመሆኑ የአያታቸዉን ይዞታ መዉረስ ይችላሉ በማለት ወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በከፊል በመሻር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1)

አጣርቶ እንዲወስን ለወረዳዉ ፍ/ቤት መልሶለታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም የከፍተኛ ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ በመቀጠል ተጠሪ ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የኦሮሚያ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን አከራክሮና መርምሮ የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት ይዞታ አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 2(16) እና 9(1) መሠረት የገጠር መሬት ይዞታ መዉረስ የሚችለዉ የቤተሰብ አባል ወይም ልጅ በመሆኑ አመልካቾች የልጅ ልጅ እንጂ ልጅ ወይም የቤተሰብ አባል ባለመሆናቸዉ የአያታቸዉን ይዞታ ሊወርሱ አይችሉም በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች የሰጡትን ዉሳኔ በመሻር የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ ሰበር አቤቱታዉም የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- በፍ/ብ/ሕ/ቁ 842(3) መሠረት የሚች የልጅ ልጆች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች በመሆናቸዉ ሚች አባታቸዉ እግር ተክተዉ አያታቸዉን የመዉረስ መብት አላቸዉ፡፡ ይህን ድንጋጌ የሻረ ሕግ በሕግ አዉጪዉ ካለመዉጣቱም በላይ ይህን በመቃወም በስር ፍ/ቤት የተነሳ ክርክር በሌለበት የስር ፍ/ቤቶች በተሳሳተ መንገድ በመተርጎም አመልካቾች የገጠር መሬት ይዞታዉን መዉረስ አይችሉም በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህትት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ የአመልካቾችም ሆነ የተጠሪ የወራሽነት ደረጃ እኩል በሆነበትና የአመልካቾች መተዳደሪያ የግብርና ሥራ መሆኑ ባላከራከረበት ሁኔታ አመልካቾችን ከዉርስ በሚነቅል መልኩ የተሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ አይደለም፡፡ የኦሮሚያ ክልል አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 9 ተተኪ ወራሽነትን አይከለክልም፡፡ አመልካቾችም በግብርና ከሚተዳደር ቤተሰብ የተወለዱና በግብርና የሚተዳደሩ እንዲሁም ሌላ የገቢ ምንጭ የሌላቸዉ መሆኑ በመረጋገጡ ከተጠሪ የሚለያቸዉ ነገር በሌለበት ተጠሪ ወራሽ ነዉ ሲባል አመልካቾች አይገባቸዉም ተብሎ የሚወሰንበት የሕግ መሠረት ባለመኖሩ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ተሽሮ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲጸናላቸዉ የሚጠይቅ ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾች አስቀድሞ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩትን አባታቸዉን ተክተዉ የአያታቸዉን የገጠር መሬት የወርስ ይዞታ እንዳይወርሱ በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ በግልጽ ክልከላ መደረግ አለመደረጉን ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመለካቾች የተጠሪ አያት ከሆኑት ከአቶ ረጋሳ ጋር ምንም ዓይነት ዝምድና ሳይኖራቸዉ አባታቸዉን ተክተዉ ለመዉረስ ያቀረቡት ጥያቄ ተገቢነት የለዉም፡፡ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ላይ አድራሻቸዉን እንደገለጹት በአዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 3 ነዋሪዎች ሲሆኑ ላለፉት 35 ዓመታት የገጠር ይዞታዎች በሚገኙበት ቀበሌ ያልኖሩ በክልሉ አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 2(16) እና 9(2) መሠረት የሚች የቤተሰብ አባል ያልሆኑ ናቸዉ፡፡ የቤተሰብ አባል የሚች ልጆች ወይም ሌላ ገቢ የሌላቸዉ በሚች ገቢ የሚተዳደሩትን የሚመለከት እንጂ የልጅ ልጅን የሚመለከት ባለመሆኑ ሚች አባታቸዉን ተክተዉ ሊወርሱ አይችሉም፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም ሰኔ 22 ቀን 2015 ዓ.ም በተዘጋጀ 6 ገጽ የሰበር አቤቱታዉን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉን መርምረን እንደተረዳነዉ ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንጻር የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ፡- አመልካቾች አስቀድሞ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩትን አባታቸዉን ተክተዉ የአያታቸዉን የገጠር መሬት የዉርስ ይዞታ እንዳይወርሱ በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ በግልጽ ክልከላ ባልተደረገበት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካቾች አባታቸዉን ተክተዉ ሊወርሱ አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

የአመልካቾች አባት የሆኑት አቶ ጫላ ረጋሳ የአመልካቾች አያት የሆኑት አቶ ረጋሳ ገቢሳ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩበት ሰኔ 15 ቀን 2010 ዓ.ም በፊት በ1984 ዓ.ም ከዚህ ዓለም ቦት መለየታቸዉ አከራካሪ አይደለም፡፡ እንዲሁም ከገጠር መሬት ይዞታ ዉጪ ያሉትን የአያታቸዉን የዉርስ ሀብት አስቀድሞ በሞት የተለየዉን አባታቸዉን አመልካቾች ተክተዉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 842(3) መሠረት የሚወርሱ መሆኑም እንዲሁ አከራካሪ አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች የተለያዩበትና አከራካሪዉ ነጥብ በገጠር መሬት የመጠቀም መብት በባህሪዉ የተለየ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 842(3) መሠረት በምትክ መዉረስ ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለዉ ነዉ፡፡

በመሠረቱ በፌዴራሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40(3) የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነዉ፡፡ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነዉ በማለት ደንግጎ የሚገኝ በመሆኑ አርሶአደሩ በገጠር መሬት ላይ ያለዉ መብት በይዞታ የመጠቀም መብት ነዉ፡፡ አንድ በገጠር መሬት ይዞታ የመጠቀም መብት ያለዉ አርሶ አደር በስጦታም ሆነ በዉርስ ሊያስተላልፍ የሚችለዉ በገጠር መሬት ይዞታዉ የመጠቀም መብቱን ነዉ፡፡ የገጠር መሬት የመጠቀም መብት እንዴት በውርስ ማግኘት ይቻላል የሚለዉን ደግሞ ከአወራሹ አርሶ አደርና ከአርሻ መሬቱ ከሚገኘው ገቢ የሚተዳደር የቤተሰብ አባል መሆን እንዳለበት የፌደራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባወጣው አዋጅ ቁጥር 456/1997 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 5 ሲደነግግ የኦሮሚያ ምክር ቤት ያወጣው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 13 እና 16 እንዲሁም አንቀጽ 9(1) ስር ማንኛዉም የገጠር መሬት ባለይዞታ በይዞታዉ የመጠቀም መብቱን በሕግ የመዉረስ መብት ላለዉ የቤተሰቡ አባል ማለትም በአርሶ አደሩ ገቢ ለሚተዳደር ወይም ለልጆቹ የማዉረስ መብት ያለዉ መሆኑን ደንግጓል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ የአርሶ አደሩ የልጅ ልጆች የቤተሰብ አባሉ እንደሆኑ ተቆጥሮ በምትክ ወራሽነት እንደሚወርሱ አልተደነገገም ወይም አልተፈቀደም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 842(3) የአርሶ አደሩ ልጅ አስቀድሞ ሲሞት የልጅ ልጆቹ በምትክ ሆነዉ የገጠር መሬት የመጠቀም መብትን የመዉረስ መብት አይኖራቸዉም፡፡

በኦሮሚያ ክልል ያለን የገጠር መሬት ይዞታ የመጠቀም መብትን በዉርስ የማስተላለፍ ጉዳይን ጨምሮ ከገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጋር ተያይዘው ለሚነሱ ክርክሮች በመርህ ደረጃ ተፈጻሚነት የሚኖራቸው የፌዴራል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 እና ይህንን አዋጅ ተከትሎ በኦሮሚያ ክልል የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 130/99 እና ደንብ ቁጥር 151/2005 እንጂ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 842(3) ምትክ ወራሽነትን ጨምሮ ጠቅላላ የዉርስ ሕግ የተመለከተዉ የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች ባለመሆናቸው በዚህ ረገድ አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም የኦሮሚያ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 2(16) እና 9(2) መሠረት አመልካቾች የሚች አያታቸዉ የቤተሰብ አባል ባለመሆናቸዉ ክርክር ያስነሱትን የገጠር መሬት ይዞታዎችን የመጠቀም መብት ሊወርሱ አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ

አልተገኘም፡፡ አመልካቾች በግብርና ስር የሚተዳደሩና ከተጠሪ የማይሉ የሚች የቤተሰብ አባል በመሆናቸዉ የገጠር መሬት ይዞታዎችን መዉርስ እንደሚችሉ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በስር ያልተነሳ ክርክር በመሆኑ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ቅሬታ አልተቀበልንም፡፡

ሲጠቃለል የኦሮሚያ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካቾች የሚች አያታቸዉ የቤተሰብ አባል ባለመሆናቸዉ ወይም የልጅ ልጆች እንጂ ልጆች ባለመሆናቸዉ የአያታቸዉን የገጠር መሬት ይዞታ የመጠቀም መብት ሊወርሱ አይችሉም በማለት የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር የአደአ በርጋ ወረዳ ፍ/ቤት ዉሳኔን በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት ባለመኖሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

1. በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 50015 የካቲት 15 ቀን 2014 ዓ.ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 395936 ሚያዚያ 11 ቀን 2014 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ የጸናዉን ዉሳኔ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 402791 ጥቅምት 22 ቀን 2015 ዓ.ም በመሻር እና የአደአ በርጋ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 46340 ታሕሳስ 21 ቀን 2014 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ለ) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ